በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ/መ/ቁ 193292

ሀምሌ 29 ቀን 2013 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡- አቶ አህመድ አብዱራህማን - ከጠበቃ ብሩክ አሰፋ ጋር ቀረቡ።

ተጠሪ፡- ኢልይስ ዲተርጀንት ኢንዱስትሪ ኩባንያ - ጠበቃ ወንድወሰን ሂርጶ ቀረቡ።

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር የውጪ ሀገር ሰው (ኩባንያ) በንግድ ምልክት ምዝገባ ላይ ያቀረበውን የተቃዉሞ አቤቱታ መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩም ጆብ (Job) እና ሂላክ (Hilaac) የተባሉ የሳሙና ንግድ ምልክቶችን ይመለከታል። የሰበር አቤቱታው በአመልካች የቀረበውም በንግድ ምልክት የተቃውሞ አቤቱታው ላይ የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በመ/ቁ 0036 በቀን 21/06/2011 ዓ.ም እንዲሁም ይግባኙ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 235010 በቀን 27/06/2012 ዓ.ም ያሳለፉት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለት ስለጠየቁ ነው።

1. ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው የአሁን አመልካች በኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በማመልከቻ ቁጥር LTM/3562/08፤ LTM/3563/08 እና LTM/3564/08 ባቀረበው የንግድ ምልክት

የምዝገባ ጥያቄ ላይ የአሁን ተጠሪ ተቃዉሞ አቅርቦ የግራ ቀኙ አቤቱታ እና ማስረጃ በሚመለከተው ሥራ ሂደት ተመርምሮ ጥቅምት 30/2009 ዓ.ም የአመልካች ጥያቄ ውድቅ ተደርጓል፡፡

2. አመልካች ይህን በመቃወም ውሳኔውን ለማስለወጥ ለአዕምሯዊ ንብረት ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታቸውን አቅርበው ነበር፡፡ የቅሬታቸው ይዘት የተቃውሞ አቅራቢው (የአሁን ተጠሪ) የውጪ ሃገር ኩባንያ በመሆኑ የውጪ ሃገር ሰዎች በአዋጁ ተቃዉሞ የማቅረብ መብት የሚያገኙት በእንካ ለእንካ መርህ ወይም ኢትዮጵያ አባል በሆነችበት ዓለም አቀፍ ስምምነት መሆኑን፤ ተጠሪ ተቃዉሞ ለማቅረብ ምንም ዓይነት መብት ወይም ጥቅም የሌለው መሆኑን፤ እንዲሁም ተጠሪ የንግድ ምልክቶቹ ባለቤት ነው መባሉ መሰረታዊ የህግ ስህተት መሆኑን የሚጠቅስ ነው፡፡

3. ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴው ፍሬ ጉዳዩን ተመልክቶ የውሳኔ ሃሳቡን ለአዕምሯዊ ጽ/ቤት ኃላፊ አቅርቧል፡፡ ኃላፊውም የውሳኔ ሃሳቡን ተቀብለው በኮሚቴው የውሳኔ ሃሳብ መሰረት ይፈፀም በማለት በመ/ቁ 00036/2009 ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኙ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 202772 ግንቦት 3/2010 ዓ.ም በዋለ ችሎት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ይግባኙን ሰርዟል፡፡

4. ከፍሲል በተጠቀሰው መልኩ በአእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በተሰጠው ውሳኔና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ባሳለፈው ትዕዛዝ ላይ አመልካች ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ቅሬታቸውን አቅርበው ጉዳዩ በሰ/መ/ቁ 158608 ታይቶ ህዳር 26/2011 ዓ.ም በዋለ ችሎት ውሳኔው ተሽሮ በመቃወሚያ ላይ ብይን ሳይሰጥ ታልፎ በፍሬ ጉዳዩ ውሳኔ መሰጠቱ አላግባብ በመሆኑ በቅድሚያ በመቃወሚያው ላይ ተገቢው ብይን እንዲሰጥበት ተመልሷል፡፡

5. ሰበር ችሎቱ ከሰጠው ውሳኔ መገንዘብ እንደተቻለው ለምዝገባ በቀረቡ የንግድ ምልክቶች ላይ ተጠሪ ተቃዉሞ የማቅረብ መብትና ጥቅም የለውም፤ እንዲሁም ተቃዉ ያቀረበው በህግ ተቃውሞ ለማቅረብ የተሰጠው ጊዜ ካለፈ በኃላ ነው በሚል አመልካች ክርክር አቅርቧል፡፡ በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/1998 አንቀጽ 3 ሥር የአዋጁን የተፈፃሚነት ወሰን በተመለከተ እንደተደነገገው በእንካ ለእንካ መርሆ ወይም ኢትዮጵያ አባል በሆነችበት ዓለም ዓቀፍ ውል ላይ በመመስረት የውጭ ሃገር ሰዎች በአዋጁ መሰረት ኢትዮጵያዊያን ያሏቸው መብቶችና ግዴታዎች እንደሚኖራቸው ተመልክቷል፡፡ ተጠሪ የውጪ ሀገር ድርጅት መሆኑ ያላከራከረ በመሆኑ መቃወሚያው ከዚሁ የህጉ ድንጋጌ አንፃር ታይቶ ሊወሰን ይገባል፡፡ በሌላ በኩል መቃወሚያው የሚቀርብበትን ጊዜ በተመለከተ የንግድ ምልክት የምዝገባ ስርዓትን በሚደነግገው የአዋጁ ክፍል ሶስት አንቀጽ 13 ሥር ስለ "ተቃውሞ"

እንደተደነገገው ማንኛውም የንግድ ምዝገባን የሚቃወም ሰው የሚቃወምበትን ምክንያት በዝርዝር በመጥቀስ በደንቡ በተወሰነው የጊዜ ገደብና የተቃውሞ አቀራረብ ሥርዓት መሰረት ማስረጃዎቹን በማያያዝና በደንቡ የተወሰነውን ክፍያ በመፈፀም ለጽህፈት ቤቱ በጽሁፍ ተቃዉሞውን ማቅረብ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 273/2005 ከአንቀጽ 26 እስከ 30 በተመለከቱት ድንጋጌዎች ሥር የተቃዉሞ ጥሪ ማስታወቂያ ስለሚወጣበት ሁኔታ፤ የንግድ ምልክት ምዝገባን ስለመቃወም፤ ስለ ተቃውሞ ማቅረቢያ ጊዜ፤ እንዲሁም በተቃውሞ ማመልከቻ ላይ ውሳኔ ስለሚሰጥበት ሁኔታ ሁሉ በዝርዝር ተደንግጓል፡፡ በአጠቃላይ የአሁኑ አመልካች በአከራካሪዎቹ የንግድ ምልክቶች ምዝገባ ላይ ተጠሪ ተቃዉሞ ማቅረብ አይችልም፤ ተቃዉሞውም የቀረበው በህግ የተፈቀደው ጊዜ ካለፈ በኃላ ነው በማለት ባቀረቧቸው መከራከሪያዎች ላይ የአዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ተጠሪ የሚያቀርበውን ክርክር ሰምቶና ማስረጃውን ተመልክቶ በህጉ አግባብ ብይን ሳይሰጥ አልፎ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ውሳኔ መስጠቱ ጉዳዩ የሚመራበትን ህግ መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ውሳኔው የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ውሳኔውን ሽሯል፡፡ ይህን ተከትሎም የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት መዝገቡን በማንቀሳቀስ አመልካች ባቀረባቸው መከራከሪያዎች ላይ ተጠሪ የሚያቀርበውን ክርክር ሰምቶና በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችለውን ተገቢ ማስረጃ መርምሮ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች አንፃር ማጣራት አድርጎ ውሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343(1) መሰረት መመለሱን መገንዘብ ይቻላል፡፡

6. በዚህ መልኩ ጉዳዩ የተመለሰለት የአዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ይግባኝ ሰሚ መዝገቡን አንቀሳቅሶ ከሰበር ችሎቱ በተያዘው ጭብጥ መሰረት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ አድርጓል፡፡ ተጠሪ በቀን 25/04/2011 ዓ.ም በሰጠው መልስ ተቃውሞ የማቅረብ መብት እንዳለው በመግለጽ በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/1998 እና አዋጁን መሰረት አድርገው በወጡት ደንብና መመሪያዎች መሰረት የውጭ ሀገር ሰዎች የንግድ ምልክት ምዝገባ ማካሄድ እንደሚችሉ፤ ጽ/ቤቱ ወደ አስራ አንድ ሺህ (11,000) የሚደርሱ የውጭ ሀገር የንግድ ምልክት ማመልከቻዎችን በመቀበል የንግድ ምልክት ምዝገባ ምስክር ወረቀት እንደሰጠ ገልጸው በዚህም መሰረት ተጠሪ በኢትዩጵያ ውስጥ ቋሚ ነዋሪ የሆነ ሰው በመወከል እና ኢትዬጵያውያን አመልካቾች ባላቸው መብት መሰረት ጠበቃ በመሰየም የንግድ ምልክቱን ምዝገባ እንደተቃወሙ ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ አክለውም የእንካ ለእንካ ስምምነት ሲነሳ መሰረት ሊያደርግ የሚገባው እስካሁን ድረስ ኢትዬጵያ የውጭ ሀገር ማመልከቻ የምትቀበል መሆኑ እና ኢትዬጵያ የሰጠችውን የምዝገባ ምስክር ወረቀት በመቀበል እዚህ የተመዘገቡ የንግድ ምልክቶች ሌሎች

ሀገሮች ላይ የሚመዘገቡ በመሆኑ ኢትዬጵያ ከሌሎች ሀገሮች የንግድ ምልክት ተቀብላ ከመመዝገብ የሚያግዳት ነገር የለም ሲሉ አቅርበዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ኢትዬጵያ ይህንን በማድረጓ ወቅቱ የሚጠይቀውን ሉላዊነት እና የውጭ ኢንቨስትመንት ፍላጎት ለማሟላት በእጅጉ ያግዛል፤ ከዚህም አልፎ ጽ/ቤቱ ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ እንዲሁም በንግድና ኢንደስትሪ ሚኒስቴር ከዛም በፊት ባሉት አመታት የንግድ ምልክት ምዝገባ ሲያካሂድ የነበረ በመሆኑ የመብት መጣበብ የሌለ ከመሆኑም በተጨማሪ ሱማሌላንድ በኢትዮጵያ የተደረገን ምዝገባ አልቀበልም ያለችበት ሁኔታ በአመልካች አልቀረበም፡፡ ኢትዬጵያ የሱማሌላንድ ምዝገባንና ተቃውሞ አልቀበልም ማለቷ ኢትዬጵያውያን በሀገሪቱ ሊኖራቸው የሚችለውን መብት የሚያስነፍግ በመሆኑ የግድ በእንካ ለእንካ መርህ መታጠር አይኖርበትም፡፡ አመልካች በክርክር ላይ ያሉትን የንግድ ምልክቶች ያሉባቸውን ምርቶች ከተጠሪ ተቀብለው ያከፋፍሉ እንደነበር ያምኑ በመሆኑ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 501/1998 አንቀጽ 7(2) መሰረት ቀዳሚ መብት ስላለው ሲጠቀምባቸው የነበሩ የንግድ ምልክቶች ለምዝገባ ሲቀርቡ የመቃወም መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ ተጠሪ የተቃውሞ ማመልከቻውን ተገቢውን ሁኔታ አሟልቶ በህጉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማለትም 60 ቀን ከማብቃቱ በፊት ያቀረበ በመሆኑ በዚህም የንግድ ምልክት ምዝገባ አዋጅንም ሆነ ደንቡን ተከትሎ የቀረበ በመሆኑ የአመልካች ክርክር ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

7. አመልካች በበኩላቸው የኢፌዲሪ ህገመንግስት ንብረት የማፍራት መብት የሚሰጠው ለኢትዮጵያዊያን መሆኑን፤ የእንካ ለእንካ ስምምነቱ እንኳን ቢኖር የውጪ ሀገር ዜጎች በኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ምልክት ምዝገባ ያካሂዳሉ እንጂ ተቃውሞ ማቅረብ ይችላሉ አይልም በማለት የቀደመ ክርክራቸውን በማጠናከር አቅርበዋል፡፡

8. ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የአእምሯዊ ጽ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ክርክሩን መርምሮ ኢትዮጵያ እና ሶማሌላንድ ግልጽ የሆነ የእንካ ለእንካ ስምምነት የላቸውም፤ ነገር ግን አሁን ባለው አለማቀፍ ልምድም ቢሆን ይህ እንዲኖር አይጠበቅም፤ የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ህጎች ከተለያዩ የአዕምሯዊ ጥበቃ ስምምነቶች ጋር የተጣጣሙ ናቸው፤ እነዚህ ስምምነቶች ደግሞ የእንካ ለእንካ መርህን ዋና አካላቸው ያደረጉ ናቸው፤ ይህን መሰረት አድርጋ ኢትዮጵያ ለውጭ ሀገር ሰዎች ዜጎችዋ ያላቸውን መብት ሰጥታ የንግድ ምልክት ምዝገባና ተያያዥ ተግባራትን ከረዥም ጊዜ ጀምሮ እያካሄደች ትገኛለች፤ ይህን በማድረጓ ዜጎቿ ሊደርስባቸው ከሚችለው የምላሽ ድርጊት (repraisal) መከላከል ችላለች፡፡ በተጨማሪም ይህን በማድረጓ ከውጪ ሀገራት የሚመጣን ኢንቨስትመንት እያበረታታች ኢኮነሚዋንም

በማሳደግ ብሔራዊ ጥቅሟን ማስከበር ችላለች። ኢትዮጵያ ለዜጎቿ የምታደርገውን ለውጪ ሀገር ዜጎችም ሆነ ድርጅቶች ማድረግ ልማድ (የውጪ አገር ንግድ ምልክቶችን የመመዝገብና የመጠበቅ እንዲሁም አገር ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ የውጪ ምልክቶች ለምዝገባ ሲቀርቡ የውጪ ዜጎች ወይም ድጅቶች የሚያቀርቡትን ተቃዉሞ የመቀበል ልምድ) ካደረገችበት ከ1978 ዓ.ም ጀምሮ ይህ አሰራር የነበረና አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በ1995 ዓ.ም ሲቋቋም የቀጠለ የረጅም ጊዜ አሰራር ነው። እስካሁን ባለው ልምድ መሰረት ሌሎች ሀገሮችም ይህንን ስለአለማድረጋቸው ከአመልካች በኩል የቀረበ ማስረጃ የለም። በመሆኑም የውጭ ሀገር አመልካቾች በእስካሁኑ የሀገሪቱ አሰራር ኢትዮጵያዊያን ያላቸው መብቶች ተጠቃሚ ሆነዋል። በተለይም ሀገሪቱ የአለም የንግድ ድርጅት አባል ለመሆን እየተንቀሳቀሰች ባለችበት ጊዜ ይህንን ማስቀጠል ተገቢ መሆኑን ይግባኝ ሰሚው ያምናል። በእነዚህ ምክንያቶች አመልካች ለምዝገባ ባቀረብኳቸው የንግድ ምልክቶች ላይ የተጠሪ ድርጅት የሚገኝበት ሀገር ከኢትዮጵያ ጋር የእንካ ለእንካ ስምምነት ስለሌለው ተቃውሞ የማቅረብ መብት የላቸውም በሚል ያቀረበው መከራከሪያ የሀገሪቱን የአዕምሯዊ ንብረት ህጎች አላማ እና የመርሁን መነሻ ሀሳብ ያላገናዘበ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም። ከዚህም ሌላ አመልካች ከተጠሪ ድርጅት ዕቃ ተቀብሎ የማከፋፈል የውል ግንኙነት እንደነበራቸው በዳይሬክቶሬቱ ተረጋግጧል፤ በተጨማሪም አመልካች ከተጠሪ ምርቱን ተቀብለው ሲያከፋፍሉ እንደነበር አስቀድሞ ካደረጉት ክርክርና በንግድ ምዝገባ ውስጥ ካሉት መረጃዎች መረዳት ይቻላል፤ ተጠሪ ከአመልካች በተጨማሪ በሌሎች ወኪሎች አማካኝነት ለክርክር የቀረቡት የንግድ ምልክቶች ያሉባቸውን ምርቶች ኢትዮጵያ ገበያ ውስጥ ሲጠቀሙበት የነበረ ስለመሆኑ ማስረጃዎች መቅረባቸው በራሱ በአዋጅ ቁጥር 501/1998 አንቀጽ 7(2) መሰረት አመልካች ምዝገባ የጠየቁበት የንግድ ምልክት በሶስተኛ ወገኖች መብት ምክንያት መመዝገብ የማይችሉ ንግድ ምልክት ውስጥ እንዲወድቅ ያደርገዋል። በመሆኑም አመልካች በማመልከቻ ቁጥር LTM/3562/08፤ LTM/3563/08 እና LTM/3564/08 ባቀረበው የንግድ ምልክት የምዝገባ ጥያቄ ላይ ተጠሪ ተቃውሞ ለማቅረብ መብትና ጥቅም አለው።

9. ሁለተኛውን ነጥብ ማለትም ተጠሪ ተቃውሞውን ያቀረበው በህግ ተቃውሞ ለማቅረብ የተሰጠው ጊዜ ካለፈ በኃላ ነው በማለት አመልካች ያቀረበውን መከራከሪያ በተመለከተም ይግባኝ ሰሚው መርምሮ የተጠሪ የተቃውሞ ማመልከቻ በስራ ክፍሉ ተፈርሞ የገባው በ16/07/2008 ዓ.ም መሆኑ መረጋገጡን፤ ዕለቱ ለፕሬስ የሚላኩ የንግድ ምልክቶች የሚዘጋጁበት እንደነበርና በዚህ ዕለት ክፍያ እንደማይፈፀም ባደረገው ማጣራት መረዳቱን፤ በዚህ ምክንያት አርብ ዕለት ላስገቡት የተቃውሞ

ማመልከቻ በሚቀጥለው የስራ ቀን ሰኞ በ19/07/2008 ዓ.ም ክፍያ እንደፈፀሙ ግንዛቤ ተወስዷል፤ ስለሆነም የንግድ ምልክቱ ለተቃውሞ ጥሪ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የወጣው በ18/05/2008 ዓ.ም ሲሆን ተጠሪ የተቃውሞ ማመልከቻውን በህጉ የተመለከተው የ60 (ስድሳ) ቀን የጊዜ ገደብ ሳያልፍ ያቀረቡ በመሆኑ በስራ ክፍሉ የውስጥ አሰራር በክፍያና ተያያዥ ምክንያቶች መብታቸው ሊታለፍ አይገባም፤ ተጠሪ የንግድ ምልክት አዋጅና ደንቡ በሚፈቅደው መሰረት ተቃውሞ እንዳቀረቡ ስለተረጋገጠ አመልካች ተቃውሞው የቀረበው በወቅቱ አይደለም በማለት ያቀረቡት መከራከሪያ ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡ በአጠቃላይ ተጠሪ በአመልካች የንግድ ምልክት ምዝገባ ጥያቄ ላይ ተቃውሞ የማቅረብ መብት አላቸው፤ እንዲሁም የተቃውሞ ማመልከቻውም በህጉ በተቀመጠ ጊዜ ውስጥ ያቀረቡ በመሆኑ የአመልካች መከራከሪያዎች ተቀባይነት ሊኖራቸው አይገባም በማለት የውሳኔ ሃሳቡን አቅርቧል፡፡

10. ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተም የውሳኔ ሃሳቡን ያቀረበ ሲሆን ከዚህም ሌላ ምርመራ እየተደረገበት ካለው ጉዳይ ጋር ግንኙነት ያለው በመሆኑ ምክንያት ጽ/ቤቱ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥበት ድረስ ቀደም ሲል በተጠሪ ስም በጽ/ቤቱ ውስጥ በማመልከቻ ቁጥር FTM/7461/2016 G.C (በምዝገባ ምስክር ወረቀት ቁጥር FTM/6277/2016) Job እንዲሁም በማመልከቻ ቁጥር FTM/7460/2016 G.C (በምዝገባ ምስክር ወረቀት ቁጥር FTM/6278/2018) Hilaac በሚል ተመዝግበው የሚገኙት የንግድ ምልክቶች እንዲታገዱ በቀን ጥር 09/2011 በቁጥር 9/6401-304/1 የተጻፈው ደብዳቤ እንዲነሳ በማለት ይግባኝ ሰሚው የውሳኔ ሃሳቡን ለአዕምሯዊ ጽ/ቤት የበላይ ኃላፊ አቅርቧል፡፡ ዋና ዳይሬክተሩም የውሳኔ ሃሳቡን ተቀብለው በውሳኔ ሃሳቡ መሰረት ይፈፀም ብለዋል፡፡

11. በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌ/ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ከፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር መ/ቁ 158608 በቀን 26/03/2011 ዓ.ም በተያዘው ጭብጥ መሰረት ክርክር ተሰምቶና ተጣርቶ በጽ/ቤቱ የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍበት የህግም ሆነ የፍሬ ነገር ምክንያት የለም በማለት ውሳኔውን አፅንቷል፡፡

12. የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች በቀን 12/01/2012 ዓ/ም ባቀረቡት ማመልከቻ ጆብ (Job) እና ሂላክ (Hilaac) የተባሉ የሳሙና ንግድ ምልክቶች ባለቤትነትን በተመለከተ ይህ ሰበር ችሎት በድጋሚ ውሳኔ እንዲሰጥበት የመለሰው የመጀመሪያ ጭብጥ ተጠሪ የሶማሌ ላንድ ድርጅት በመሆኑ የእንካ ለእንካና አለም አቀፍ ስምምነት በሌለበት ሁኔታ ተቃውሞ የማቅረብ መብት የሌለው ሆኖ ሳለ ጽ/ቤቱና የስር ከፍተኛ ፍ/ቤት መብት አለው በሚል ውሳኔ መስጠታቸው መሰረታዊ የህግ

ስህተት ነው፡፡ በህገ መንግስቱና አግባብነት ባላቸው ህጎች የተገለጸውን እንዲሁም ትክክለኛ ልማዶችን ወደ ጎን በመተው ያለምንም ስምምነት ከ1978 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዬጵያ ከ11 ሺህ በላይ ለውጭ ሀገር ዜጎች (ድርጅቶች) የአእምሯዊ ንብረት ጥበቃ ሲደረግ እንደነበር በሀሰት በማረጋገጥ የሶማሌ ላንድ ድርጅት የሆነው ተጠሪ ተቃውሞ የማቅረብ መብት አለው በሚል የንግድ ምልክቶቹ ለተጠሪ እንዲመዘገቡ ውሳኔ መስጠታቸው አግባብ አይደለም፡፡ በየትኛውም መመዘኛ ከታየ አንድ አለም አቀፍ ስምምነት ተፈጻሚነትና አስገዳጅነት የሚኖረው ስምምነቱን ፈርመው ባጸደቁት አባል ሀገራት መካከል ነው፤ ኢትዬጵያ ለውጭ ሀገር ሰዎች (ድርጅቶች) የንግድ ምልክትን ጨምሮ በአጠቃላይ የአእምሯዊ ንብረት ጥበቃ የምታደርገው ፈርማ ባጸደቀችው አለም አቀፍ ስምምነት መሰረት ነው፡፡ ጽ/ቤቱ ያለስምምነት ጥበቃ ያደረገው እስከማውቀው ድረስ ለተጠሪ ብቻ ነው፡፡ ሰበር ችሎት መዝገቡን ሲመልስ በሁለተኛነት የያዘውን ጭብጥ በተመለከተም ከፍተኛ ፍ/ቤትና ጽ/ቤቱ ተጠሪ ተቃውሞውን ያቀረበው በሕጉ በተቀመጠው ጊዜ ካለፈ በኋላ ቢሆንም ተቃውሞ የማቅረብ መብት አለው በሚል የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ የጽ/ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴና ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኝ ያቀረቡትን ማስረጃዎችና ክርክሮች በህግ አግባብ ሳይመረምሩና ለውሳኔያቸው ሳይጠቀሙ ማለፋቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ በመሆኑም የሰጡት ውሳኔ እንዲሻርልኝና አመልካች ለምዝገባ ያቀረብኩት ጆብና ሂላ የተባሉ የንግድ ምልክቶች ላይ ተጠሪ ተቃውሞ የማቅረብ መብት የለውም፤ እንዲሁም የአእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ጆብና ሂላክ የተባሉ የንግድ ምልክቶች ለአመልካች እንዲመዘግብ ውሳኔ እንዲሰጥልኝ በማለት ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡

13. ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ አመልካች ባቀረበው የንግድ ምልክት ባለቤትነት ምዝገባ ተጠሪ ተቃውሞ የማቅረብ መብት አለው ተብሎ የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ከንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 3 እና 13 እንዲሁም ከደንብ ቁጥር 273/2005 አንቀጽ 27(2) አኳያ ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡

14. ተጠሪ በቀን 20/02/2013 ዓ.ም ባቀረበው መልስ የንግድ ምልክት አዋጁ በአንቀጽ 3 የተፈጻሚነት ወሰኑን ሲገልጽ በእንካ ለእንካ መርህ ወይም ኢትዬጵያ አባል በሆነችበት አለም አቀፍ ውል ላይ በመመስረት የውጭ ሀገር ዜጎች ኢትዬጵያውያን ያሏቸው መብትና ግዴታቸው እንደሚኖራቸው ይደነግጋል፡፡ ከዚህ የህጉ እሳቤ ተነስተን የእንካ ለእንካ መርህን ሀገሪቱ ከፈረመቻቸው አለምአቀፍ ውሎች ነጥለን ማየት ይኖርብናል፡፡ እንደ ህጉ አንቀጽ የእንካ ለእንካ መርህ የውጭ ሀገር ዜጎች

ኢትዬጵያውያን ያሏቸውን መብትና ግዴታ የሚያጎናጽፍ አንዱ መርህ ሲሆን ሀገሪቱ የምትፈራረማቸው አለም አቀፍ ውሎች ደግሞ ሌላው መብት የማግኛ ግንኙነት ስለመሆናቸው ሁለቱ መብት ሰጪ መስፈርቶች ወይም በሚለው አያያዥ ቃል መቅረባቸው ያስረዳል፡፡ የእንካ ለእንካ መርህ የኢትየጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በተግባር እየሰራበት እንዳለውም ሆነ የህጉ አግባብ እንደሚያስረዳው ስምምነቱ በፊርማ የሚከወንና በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ሀገራት ድርድር የሚቀመጡበት መርህ አይደለም፡፡ ከዚህ ይልቅ አንዱ ሀገር ለሌሎች ሀገራት ዜጎች በሚሰጠው መብት ልክ ለዜጎቹም በሌላ ሀገር በምላሹ እንዲሰጥ በሚያስችለው ነው፡፡ ነገር ግን አመልካች ከዚህ አለም አቀፍ መርህ ጋር ባልተጣጣመ መልኩ ትርጉም በመስጠት በንግድ ምልክት አዋጁ እንኳ ከአለም አቀፍ ውሎች ተነጥሎ የቀረበውን የእንካ ለእንካ መርህ ጽንሰ ሀሳብ በደምሳሳው አንድ አድርጎ በመውሰድ ያቀረቡት መከራከሪያ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡ አመልካች ሱማሌላንድ እንደ ሀገር ስለማትቆጠር አለም አቀፍ ስምምነት ልትፈርም አትችልም ያሉትን በተመለከተ አንድን ሀገር እንደ ሀገር መቁጠር ከኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ይልቅ ፖለቲካዊ ግንኙነት እንደሆነ በመስኩ የዳበሩ ጽሁፎች ያስገነዝባሉ፤ አሁን ክርክር እየቀረበ ያለው ኢትዬጵያ ለሱማሌላንድ የፖለቲካ እውቅና ሰጥታለች አልሰጠችም አይደለም፤ ይህ ቢታለፍ እንኳ አለም አቀፍ ስምምነት ለመፈረም እንደ ሀገር መቆጠር አለበት ቢባል እንኳ ሱማሌ ላንድ የሱማሊያ ሀገር አካል እንደሆነች የታወቀ ነው፡፡ አሁን ባለው ሁኔታ የሱማሌ አካል በመሆኗ ኢትዬጵያ ግንኙነት እያደረገች ያለችው በአለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ካለው ከሱማሊ ሀገር ጋር ነው፡፡ ሱማሊያ ደግሞ የአለም አቀፍ ስምምነት መፈረምም ሆነ የሀገሮች የዳበረ ልምድ የሚገዛት ሀገር ነች፡፡ ተጠሪ የሱማሌላንድ ድርጅት በመሆኑ በሁለቱ ሀገራ መሀከል ስምምነት በሌለበት ሁኔታ የንግድ ምልክት ምዝገባዬን ለመቃወም መብት አለው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ስህተት ነው የሚለውን መከራከሪያ በተመለከተ ይህ ነጥብ በጥቅሉ የውጭ ሀገር ዜጋ በኢትዬጵያ ውስጥ ንብረት የማፍራትና ይህንኑም በሀገሪቱ ህግ መሰረት የማስጠበቅ መብት ያለው መሆን አለመሆንና እንዲህ ያለ መብትም ማግኘት የሚቻለው ሀገራት በፈረማቸውና ባጸደቁት የእንካ ለእንካ መርህ ወይም አለም አቀፍ ስምምነት መሰረት ብቻ ስለመሆኑ ነጣጥሎ ማየት ያስፈልጋል፡፡ በንግድ ምልክት አዋጁ አንቀጽ 4 እና 7 እንደተቀመጠው የንግድ ምልክት ባለቤትነት አንድም በማስመዝገብ በሌላም በኩል በሀገር ውስጥ ጥቅም ላይ በማዋል ባለቤትነት እንደሚገኝ ይደነግጋል፡፡ ከእነዚህ ከሁለቱ ባንዱ የባለቤትነት መብት ያገኘ ሰው በንግድ ምልክቱ ላይ የቀዳሚነት መብት ይኖረዋል፡፡ የዚህ ህግ መርህ የንግድ ምልክቱን ባለቤት ዜግነት የሚከተል ሳይሆን የሸማቹን ህብረተሰብ፣ የገበያ ስርአቱንና

የንብረት መብቱን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ የውጭ ሀገር ሰው ንብረት የማፍራትም ሆነ የአእምሯዊ ንብረት ባለቤት መሆን ህጋዊ መብቱ መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ በሀገሪቱ ህግ መሰረት ባለንብረትነት በሚሰጠው መብት ልክ ንብረቱን የመጠቀም፣ የማስተላለፍ እንዲሁም የመጠበቅ መብት አብሮ እንደሚኖረው መረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች የተጠሪ የንግድ ወኪል በመሆን በኢትዬጵያ ገበያ ውስጥ በተጠቀሱት የንግድ ምልክቶች መለያነት የሚቀርቡትን የዱቄት ሳሙና ምርቶች ሲያከፋፍሉ እንደነበር በስር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ነው፤ የውክልና ስልጣኑም ምርቶቹን የመሸጥ እንጂ በንግድ ምልክቶቹ ላይ አንዳችም መብት የሚፈጥርለት አለመሆኑ ይታወቃል፤ ስለሆነም አመልካች እነዚህን የንግድ ምልክቶች ያለባለቤቱ ያለ ተጠሪ ፈቃድ መጠቀም እንዲሁም በራሱ ስም የማስመዝገብ ሂደትን ተጠሪ የመቃወም ህጋዊ መብት አለው፡፡ በሌላም በኩል ተጠሪ የመቃወሚያ ማመልከቻውን መጋቢት 16/2008 ዓ.ም ጊዜው ከማለፉ ከሁለት ቀናት በፊት አቅርቧል፡፡ በመሆኑም የኢትዬጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት እንዲሁም ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ እንዲጸና በማለት ተከራክሯል፡፡  አመልካችም በመልስ መልሳቸው አቤቱታቸውን በማጠናከር አቅርበዋል፡፡

15. ከፍ ሲል በአጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ነው፡፡ በበኩላችን ለሰበር ችሎቱ የተያዘውን ጭብጥ ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

16. በሰበር አጣሪ ችሎቱ እንዲታይ የተያዘው ጭብጥ አመልካች ያቀረበውን የንግድ ምልክት ባለቤትነት ምዝገባ ተጠሪ የውጭ ሀገር ኩባንያ ከመሆኑ አንፃር ሊቃወም መቻሉን የተመለከተ ሆኖ ጉዳዩን በተለይ ከንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 3 እና 13 እንዲሁም ከደንብ ቁጥር 273/2005 አንቀጽ 27(2) አኳያ ያለውን እንድምታ ለመመርመር ነው፡፡

17. ይህን ጭብጥ ለመወሰን የአዋጁን የተፈፃሚነት ወሰን የሚደነግገውና *በእንካ ለእንካ መርሆ* ወይም *ኢትዮጵያ አባል በሆነችበት ዓለም ዓቀፍ ውል* ላይ በመመስረት የውጭ ሃገር ሰዎች በአዋጁ መሰረት ኢትዮጵያዊያን ያሏቸው መብቶችና ግዴታዎች እንደሚኖራቸው የተመለከተው ድንጋጌ ሊተረጎም የሚገባበትን ሁኔታ በህጉ ከተዘረጋው የንግድ ምልክት ምዝገባ አላማና በዘርፉ ከዳበረው አለማቀፍ እንዲሁም ሀገራዊ ልምድ አንፃር መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡

18. ከፍሲል ከተጠቀሰው የአዋጁ ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለው የእንካ ለእንካ መርህ የሀገሪቱ ህግ አካል በመሆኑ እንዲሁም ሀገሪቱ አባል የሆነችበት አለማቀፍ ስምምነት ሲኖር የውጭ ሀገር ዜጎች እንዲሁም ኩባንያዎቻቸው ኢትዮጵያዊያን የንግድ ምልክት በማስመዝገብ፣ ለምዝገባ የቀረበን የንግድ ምልክት

በመቃወም በአጠቃላይ ኢትየጵያዉያን ያላቸው መብቶችና ግዴታዎች የውጪ ዜጎችም እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

19. የእንካ ለእንካ መርህ (principle of reciprocity) በዘርፉ የሚታወቅ ሲሆን መርሁ የሚይዘው ትርጉም "አንተ ባደረክግልኝ መጠን እኔም አደርግልሃለሁ" እንዲሁም "እኔ ባደረኩልህ መጠን አንተም ታደርጋለህ" የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ ይህን መርህ ተጠቅመው ሃገራት ጥቅማቸውን ያስከብራሉ የሌሎችንም ጥቅም በዚያው መጠን ያከብራሉ፡፡ ይህ የእንካ ለእንካ መርህ የ"ናሽናል ትሪትመንት" (National Treatment) አካል ሲሆን የ"ናሽናል ትሪትመንት" መሰረተ ሃሳብ የአለማቀፍ ልማዳዊ ህግን መሰረት የሚያደርግ ሆኖ በሃገራቱ መካከል ግልፅ የሆነ ስምምነት ባይኖር እንኳ አንድ ሀገር ለሀገሩ ዜጎች የሚያከብረውን መብት እና የሚጥለውን ግዴታ ለሌሎች ሀገሮች ዜጎችም በተመሳሳይ እንደሚያደርግ የሚያስገነዝብ ነው፡፡

20. በሌላም በኩል አለማቀፍ ስምምነቶችን በተመለከተ የንግድ ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ እና ሌሎች በስራ ላይ ያሉ የሀገሪቱ አዕምሯዊ ንብረት ህጎች ከአለማቀፍ ስምምነቶች ጋር የተጣጣሙ ሆነው ይታያሉ፡፡ የሀገሪቱ የአዕምሯዊ ንብረት ህጎች ዝቅተኛ የስምምነት ስታንዳር ከሚያስቀምጠው ከአለማቀፉ "ንግድ ነክ የሆኑ የአእምሯዊ ንብረት ስምምነቶች" (Trade Related Intellectual Properties Agreement – በአጭሩ "TRIPS Agreement") ጋር ስምም የሆኑ ድንጋጌዎችን የያዙ መሆኑ ሲታይ ሀገሪቱ ለውጭ ሀገር ሰዎች የአእምሯዊ ንብረት አለማቀፍ ስምምነቶችን መሰረት ባደረገ መልኩ ተገቢ ጥበቃ የምታደርግ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

21. ከንብረት መብት አንጻርም የውጪ ሀገር ሰዎች የአእምሯዊ ንብረትን ጨምሮ በአጠቃላይ የንብረት መብታቸው በኢትዮጵያ የሚከበርበትን አግባብ መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ አለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ (UDHR) አንቀጽ 17 ማንኛውም ሰው በራሱም ሆነ ከሌሎች ጋር በማህበር የንብረት ባለቤት የመሆን መብቱ እንደሚከበር እና ያለአግባብ ንብረቱን ሊነጠቅ የማይችል ስለመሆኑ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአለም አቀፍ የኢኮኖሚ የማህበራዊና ባህላዊ ስምምነት ሰነድ (ICESCR) አንቀጽ 15 በተመሳሳይ መልኩ በመደንገግ ለንብረት መብቱ ጥበቃ ያደርጋል፤ በአባል ሀገራትም ላይም ኃላፊነት ይጥላል፡፡ እነዚህ አለም አቀፍ ስምምነቶች ኢትዮጵያ የፈረመቻቸውና ያጸደቀቻቸው በመሆኑ በሕገመንግስቱ አንቀጽ 9(4) እና አንቀጽ 13(2) መሰረት የሀገሪቱ ህግ አካል ናቸው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የውጭ ሀገር ሰዎች (የሕግ ሰውነት ያላቸውን ጨምሮ) በሀገሪቱ ንብረት የማፍራት እና ባለቤት የመሆን መብት አላቸው፡፡ በተለይ አእምሯዊ ንብረት በባህሪው ድንበር ተሻጋሪ ሲሆን የሁሉም ሀገራት ዜጎች

ጥቅምና ፍላጎት የሚንፀባረቅበት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የአእምሯዊ ንብረትን የተመለከቱ ህጎች የሚፈፀሙበት እና የሚተረጎሙበት አግባብ የውጭ ሀገር ዜጎች በኢትዬጵያ ንብረት የማፍራትና ባለቤት የመሆን መብት ያላቸው መሆኑን ታሳቢ በማድረግ ሊሆን ይገባል፡፡

22. ከዚህም ሌላ የአለም አቀፍ ሕግንና አለማቀፍ ስምምነቶችን የሚመለከቱ ክርክሮች ሲነሱ የህጎቹ ምንጭ ተያይዞ ሊታይ ይገባል፡፡ የአለማቀፍ ህግ ምንጮች ተደርገው የሚወሰዱት የመጀመሪያው (Primery Source) አለም አቀፍ ስምምነቶች፣ በዘርፉ የዳበረው አለም አቀፍ ልማድ፤ እና በአለም አቀፍ ሕጎች እውቅና የተሰጣቸው አጠቃላይ መርሆች ሲሆኑ በቀጣይነት (Secondary Source) የፍርድ ቤት ውሳኔዎች፤ የታዋቂ ምሁራን አስተያየት እና ጽሁፎች ሁሉ ይገኙበታል፡፡ ይህም በአለም አቀፍ ፍ/ቤት መቋቋሚያ ሕግ (Statute of International Court of Justice) አንቀጽ 38(1) ስር ተመልክቷል፡፡ በዚህም አገሮች አለምአቀፍ ስምምነቶችን ባይፈርሙም ከላይ በተመለከተው አኳኋን የአለም አቀፍ ስምምነቶቹ ላይ የተመለከቱት መብትና ግዴታዎች አለምአቀፋዊ ልማድ ከሆኑና በብዙ አገራት ወጥነት ባለውና በዳበረ ሁኔታ የሚተገበሩ ከሆነ ባልፈረሙት ሀገራት ጭምር ተፈጻሚ የሚሆኑ መሆናቸውን ያስገነዝበናል፡፡

23. በተለይ ከአእምሯዊ ንብረት መብት እና በልዩ ሁኔታም ከንግድ ምልክት ጋር በተያያዘም የ WTO እና TRIPS ስምምነት፤ እንዲሁም የበርን ኮንቬንሽን (Berne Convention)፣ የፓሪስ ኮንቬንሽን (Paris Convention)፣ እና የማድሪድ ፕሮቶኮል (Madrid Protocol) የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እነዚህና መሰል የአለም አቀፍ ስምምነቶች የሚመሩበት መሰረታዊ መርህ ብሄራዊ ስምምነት ሲሆን ለአንድ ሀገር ዜጎች የሚጠበቀው መብት ወይም የሚጣለው ግዴታ በሌሎች ሀገሮች ዜጎችም ያለ አድሎ በእኩልነት ተፈጻሚነት እንዲኖረው የሚገባውን ግዴታ የሚመለከት ነው፡፡ ይህም ለአብነት በ TRIPS አለምአቀፍ ስምምነት አንቀጽ 3 ስር ተመልክቶ ይገኛል፡፡ ስለሆነም ሀገራት ለውጭ ሀገር ዜጎች ጨምሮ የአእምሯዊ ንብረት መብት ጥበቃ የሚያደርጉ ሲሆን የሚሰጠው ጥበቃ አይነትና ተፈጻሚነት ግን የአለም አቀፍ ስምምነቶች አባል በሆኑት እና የሁለትዬሽ እና አህጉራዊ ስምምነቶችን ባጸደቁ ሀገራት የተሻለ ሆኖ ይታያል፡፡ አንዳንድ ሀገራት ደግሞ አብዛኞችን አለም አቀፍ ስምምነቶች ሳያጸድቁ ነገር ግን የአእምሯዊ ንብረት መብቶችን የተመለከቱ አለማቀፋዊ መርሆችና አሰራሮችን በሀገራቸው ህጎች ደንግገው ይገኛሉ፡፡ በዚህ መልኩ ለመብቱ ጥበቃ ከሚያደርጉ ሀገራት መካከል ኢትዬጵያ አንዷ ስትሆን አዋጅ ቁጥር 501/98 እና ሌሎቹ የአእምሯዊ ንብረት አዋጅና ደንቦች ይህን የሚያሳዩ ናቸው፡፡

24. ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ኢትዮጵያ ከሱማሌላንድ ጋር ግልጽ የሆነ የእንካ ለእንካ ስምምነት የላትም። ከሱማሌላንድ ሁኔታ እና ከፍሲል ከተመለከተው አለማቀፉ ልምድ እንዲሁም ከሀገራችን የአእምሯዊ ንብረት ህጎች አለማና ይዘት አንፃርም ቢሆን ስምምነቱ እንዲኖር አይጠበቅም። ፍሬ ነገርን የማጣራት ስልጣን ያላቸው የስር ፍርድ ቤት እና ይግባኝ ሰሚው አካል እንዳረጋገጡት ሀገሪቱ ለውጪ ሀገር ሰዎች ዜጎቿ ያላቸውን መብትና ግዴታ በተመሳሳይ በማወቅ የንግድ ምልክት ምዝገባና ተያያዥ ተግባራትን ከረዥም ጊዜ ጀምሮ ስታካሂድ ኖራለች። ኢትዮጵያ ለዜጎቿ የምታደርገውን ለውጪ ሀገር ዜጎችም ሆነ ድርጅቶች በማድረግ የውጪ ሀገር ንግድ ምልክቶችን የመመዝገብና የመጠበቅ እንዲሁም አገር ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ የውጪ የንግድ ምልክቶች ለምዝገባ ሲቀርቡ የውጪ ዜጎችና ድርጅቶች የሚያቀርቡትን ተቃውሞ ተቀብሎ የማስተናገድ ልምድ ከ1978 ዓ.ም ጀምሮ የነበረ መሆኑና አሁንም በአዕምሯዊ ጽ/ቤት የቀጠለ ልምድ መሆኑ ተረጋግጧል። ይህን ማድረጓም የውጭ ሀገር እንቨስትመንት በሀገሪቱ እንዲስፋፋ የሚያበረታ መሆኑና ዜጎቿ በሌሎች ሃገራት ሊደርስባቸው ከሚችለው የምላሽ ድርጊት (repraisal) የሚታደግ መሆኑም ተመልክቷል።

25. ከዚህም ሌላ አመልካች ከተጠሪ ድርጅት ጋር ዕቃ ተቀብሎ የማከፋፈል የውል ግንኙነት የነበራቸው መሆኑ፤ ከዚህ ጋር በተያያዘ አመልካች ለዳይሬክቶሬቱ የውክልና ውል መቋረጡን የሚገልጽ ደብዳቤ ያስገቡ መሆኑ፤ እንዲሁም አመልካች ከተጠሪ ምርቱን ተቀብለው ሲያከፋፍሉ እንደነበር በአእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ሥር በተደራጀው ዳይሬክቶሬት መረጋገጡ እና አስቀድሞ ግራቀኙ ያደረጉት ክርክር ይህንኑ እንደሚያሳይ በፍሬ ነገር ደረጃ በህግ ስልጣኑ በተሰጣቸው አካላት መረጋገጡን ተገንዝበናል።

26. ከፍሲል እንደተገለፀው በኢትዬጵያ አእምሯዊ ጽ/ቤትም ሆነ በቀደሙ የሀገሪቱ ተቋማት ከ1978 ዓ.ም ጀምሮ የውጭ ሀገር ዜግነት ላላቸውን ከ11,000 (አስራ አንድ ሺህ) በላይ ለሆኑ በውጭ ለተቋቋሙ ድርጅቶች ለዜጎች እንደሚደረገው ሁሉ መብታቸው እንደተጠበቀላቸው መረጋገጡ በዚህ ረገድ በሀገሪቱ የዳበረ ልምድ ያለ ስለመሆኑ ያሳያል። ይኸውም በአለምአቀፍ ደረጃ የዳበረው ልምድ የሀገሪቱ የህግ አካል መሆኑን ስለሚያሳይ ተጠሪ የተረጋገጠ መብት እያላቸው መብታቸው ሲነካ ተቃውሞ ማቅረብ አይችሉም የሚባልበት የህግ ምክንያት አለመኖሩን የሚያስገነዝብ ነው።

27. ስለሆነም አመልካች ለምዝገባ ባቀረባቸው የንግድ ምልክቶች ላይ ተጠሪ ተቃውሞ የማቅረብ መብት የለውም በሚል የቀረበው መከራከሪያ የሀገራችንን አእምሯዊ ንብረት ህጎች አላማና ይዘት፣ የእንካ ለእንካ መርህ ጽንሰ ሃሳብና አተገባበሩን፤ አለማቀፍ ህጉን ፤ እንዲሁም ሀገሪቱ ለረዥም ዘመን ስትሰራበት የኖረችውን ልምድ መሰረት ያደረገ ሆኖ አላገኘነውም። በመሆኑም መከራከሪያው ውድቅ

ተደርጎ ተጠሪ መቃወሚያውን ማቅረብ ይችላል ተብሎ በመወሰኑ የተፈፀመ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

28. ሌላው የአመልካች ክርክር ተጠሪ ተቃዉሞውን ያቀረበው በህግ ተቃውሞ ለማቅረብ የተሰጠው የ 60 ቀናት ጊዜ ካለፈ በኃላ ነው የሚል ነው፡፡ አከራካሪውን የንግድ ምልክት ምዝገባ በተመለከተ የንግድ ምልክቱ ለተቃውሞ ጥሪ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የወጣው በ18/05/2008 ዓ.ም ነው፡፡ በጉዳዩ ላይ የግራቀኙ ክርክርና ማስረጃ በይግባኝ ሰሚው ተመርምሮ የተጠሪ የተቃውሞ ማመልከቻ በስራ ክፍሉ ተመዝግቦ የገባው በህግ የተመለከተው ጊዜ ሳያልፍ አርብ ዕለት በ16/07/2008 ዓ.ም መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ዕለቱ ለፕሬስ የሚላኩ የንግድ ምልክቶች የሚዘጋጁበት ስለነበር በዚህ ዕለት ተቋሙ ክፍያ የሚቀበልበት ሁኔታ ባለመኖሩ ተጠሪ አርብ ዕለት ላስገባው የተቃውሞ ማመልከቻ በሚቀጥለው የስራ ቀን ማለትም ሰኞ በ19/07/2008 ዓ.ም ክፍያ እንደፈፀመ ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም የንግድ ምልክት አዋጅና ደንቡ በሚፈቅደው መሰረት ተጠሪ የተቃውሞ ማመልከቻውን በህጉ የተመለከተው የ60 (ስድሳ) ቀን የጊዜ ገደብ ሳያልፍ ያቀረበ መሆኑ ተረጋግጦ በስራ ክፍሉ የውስጥ አሰራር ምክንያት ክፍያ በሚቀጥለው የስራ ቀን በመከፈሉ የመቃወም መብታቸው ሊታለፍ አይገባም ተብሎ የአመልካች መከራከሪያ ተቀባይነት ማጣቱ ህጉንና የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

29. በአጠቃላይ የእንካ ለእንካ መርህ (principle of reciprocity) በሀገራት መካከል ግልፅ የሆነ ስምምነት ባይኖርም እንኳ አንድ ሀገር ለሀገሩ ዜጎች የሚያከብረውን መብት እና የሚጥለውን ግዴታ ለሌሎች ሀገሮች ዜጎችም በተመሳሳይ እንደሚያደርግ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 3 ሥር የተመለከተው የእንካ ለእንካ መርህ ሊተረጎም የሚገባውም ሌላው ሀገር ለዜጎቹ የሚያደርገውን የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ ለኢትዮጵያዊያን የማያደርግ ከሆነ የዚያ ሀገር ዜጎችም ሆነ ድርጅቶች በኢትዮጵያ የንግድ ምልክታቸው እንዲመዘገብና ጥበቃ እንዲደረግላቸው ለመጠየቅ እንዲሁም የተያያዥ መብቶች ተጠቃሚ ሊሆኑ አይችሉም ተብሎ ነው ብለናል፡፡

30. በተያዘውም ጉዳይ በኢትዮጵያ ምዝገባና ጥበቃ የተደረገላቸው የንግድ ምልክቶች በሶማሊያ ጥበቃ እንደማይደረግላቸው በአመልካች በኩል የቀረበ ክርክርና ማስረጃ ባለመኖሩ፤ የሀገራችን የንግድ ምዝገባና ጥበቃ አዋጅም ሆነ ሌሎች የሀገሪቱ አዕምሯዊ ንብረት ህጎች ከአለማቀፍ ስምምነቶች ጋር የተጣጣሙ ሆነው የተቀረፁ በመሆኑ፤ ሀገሪቱ ለውጪ ሀገር ሰዎች ዜጎቿ ያላቸውን መብትና ግዴታ

በተመሳሳይ በማወቅ የንግድ ምልክት ምዝገባና ተያያዥ ተግባራትን ከረዥም ጊዜ ጀምሮ ስታካሂድ የኖረች መሆኑም የተረጋገጠ በመሆኑ፤ እንዲሁም ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 ከተሰጠው መሰረታዊ የህግ ስህተትን የማረም ስልጣን አንጻር የፍሬ ነገር ክርክርና ማስረጃን የሚመለከት ባለመሆኑ ምክንያት አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡ ተጠሪ አከራካሪውን የንግድ ምልክት በተመለከተ መቃወሚያውን ማቅረብ ይችላል፤ መቃወሚያውም የቀረበው በህጉ በተፈቀደው ጊዜ ውስጥ ነው ተብሎ በመወሰኑ የህግ ስህተት ያልተፈፀመ በመሆኑ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በመ/ቁ 0036 በቀን 21/06/2011 ዓ.ም እንዲሁም ይግባኙ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 235010 በቀን 27/06/2012 ዓ.ም ያሳለፉት ውሳኔ መሰረታዊበፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/98 አንቀጽ 3 ሥር የተመለከተው "የእንካ ለእንካ" መርህ ሊተረጎም የሚገባው ሌላው ሀገር ለዜጎቹ የሚያደርገውን የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ ለኢትዮጵያዊያን የማያደርግ ከሆነ "የውጭ ሀገር ሰዎች" በኢትዮጵያ የንግድ ምልክታቸው እንዲመዘገብና ጥበቃ እንዲደረግላቸው ለመጠየቅ እንዲሁም የተያያዥ መብቶች ተጠቃሚ ሊሆኑ አይችሉም ተብሎ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት እና ለአእምሯዊ ጽ/ቤት ይተላለፍ፡፡
6. ውሳኔው ነሀሴ 10 ቀን 2013 ዓ.ም በችሎት ተነቧል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ሄ/መ                የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡